# <u>የፖለቲካ ሽሙጥ</u>

*ከአስተዋይ በቀለ*

የአዲስ አበባው ቅዱስ ሲኖዶስ መንፈስ ሊቀርበው ነው መሰል የማይበገረውን የዳቢሎስ ሸንጋይ አጋለጠ።

ለጊዜው ከፖለቲካው ደቱር እናድርግ። ቅዱስ መጽሐፍ የእግዚአብሔርን ቃል የነጠረ ነው ይላል። ልባቸውና ጆሮአቸው ያልተገረዘ አንዳንድ አንገተ ደንዳና የቤተ ክርስቲያን ሰዎች ግን፤ ቃሉን ችላ እያሉ በመንፈስ አይመሩም። ፅድቅና ቅድስናን አይላበሱም። በዘመናት ታሪክ ውስጥ የጠበቅናትን እምነትና ቤተ ክርስቲያን ያረክሳሉ።

እስቲ ፍረዱ። ጅንስ ከውስጥ ታጥቆ ከሽጋዋ ቢያንሴ ጋር ጎን ለጎን ተቀምጦ ፈንዘክ ማለት ምን ይሉታል?

ድሮ በዚያ ከግብፅ በተላከ አቡን የጠላነው አንሶ ካፌ ላቴ ግጥም አድርጐ ጠጥቶ ቅዳሴ መግባትስ ምን ይባላል?

የቤተ ክርስቲያን መሪ ፅድቅንና መንግስተ ሰማያትን ይመኛል እንጂ፤ ሀብታም ሰፈር ቦሌ መድኃኔዓለም ቅጽር ግቢ ውስጥ ሐውልቱን ያሰራል?

ስንቱን ያወረደችና ያዋረደች በሊላ መለኰንን ቅዱስ ፓትርያርክ መኖሪያ ቤት እያስገቡ ፈላጭ ቆራጭ ማድረግ ምን ይሉታል?

የሃይማኖት መሪ እግዚአብሔርን በመምሰል ፍጹምና የጸና፤ በጐ ሥራ የሚሰራ፤ ከሥጋ ፍላጎት፣ ከአፀያፊና ከአመጽ የራቀ፤ ሥራው፣ ባሕሪውና መኘታው ንፁሕ የሆነ፤ ከዘረኝነትና ከፖለቲካ የፀዳ፤ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን የማያረክስ፣ ቅሌታም ያልሆነ መሆን አለበት።

አባታችንስ እንዲያው የወያኔ ያልተራገፈ ጭነት ናቸው። አንድ ቀን ያለ ፓስፖርትና ቪዛ ሰተት ብለው ገሃነመ -እሳት ይገባሉ። መንገዱን ጨርቅ ያድርግላቸው። ሃሌ ሉያ !
እግዚ አብሔር ታላቅ ነው።

ወያኔ ያተራመሰው አገርና ሕዝብን ብቻ ሳይሆን ቤተ ክርስቲያንንም ጭምር ነው።

ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ቁንጮው ከተጋለጠ ወያኔም ይቀጥላል። ሁለቱም ተያይዘው ጀሃነም ይገባሉ። ያኔ ቤተ ክርስቲያንም አገርም ነፃ ይወጣሉ።